**ደንብ ቁጥር፡ 227/2014**

## የኦሮሚያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ምክር ቤት እና ሴክሬታሪያት ለማቋቋም የወጣ ደንብ

የግብርና ልማት ሥራዎች በክልሉ እንዲካሄዱ ለመደገፍ እና በክልሉ የሚሰራ የግብርና ትራንስፎርሜሽን ቅንጅት ባለው መልኩ ለማካሄድ ይህንን ተግባር በበላይነት የሚመራ አካል ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ፤

በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት አስፈጻሚ አካላት አዋጅ ቁጥር 242/2014 አንቀጽ 73 (1) መሠረት ይህ ደንብ ወጥቷል።

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

ደንቡ "**የኦሮሚያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ምክር ቤት እና ሴክሬታሪያት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር** 227/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡ -

1) "**ድርጅቶች**" ማለት የፌዴራልና የክልል የመንግስት ድርጅቶች፣ የግብርና ምርምር እና ልማት ሥራዎችን ለማካሄድ በሕጉ መሰረት የተቋቋሙ ወይም ሥልጣን የተሰጣቸው ዩኒቨርሲቲዎች፣ የመንግስት ወይም የግል ድርጅቶች ማለት ነው።
2) "**ኢንስቲትዩት**" ማለት የኦሮሚያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ማለት ነው።
3) "**ክላስተር**" ማለት የሥነምህዳር ሁኔታ (ኢኮሎጂ)፣ የግብርና ምርት አይነት እና የመሬት አቀማመጥን መሠረት በማድረግ የግብርና ትንስፎርሜሽን ሥራ ለማካሄድና የግብርና ምርምር እና ልማት ሥራ ማስተባበር እና ማገዝ በሚያስችል መልኩ የክልሉ ዞኖች፣ በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የምርምር ተቋማት እና ዩኒቨርሲቲዎች ተከፋፍለው የሚመደቡበት ሁኔታ ነው።
4) "**ምክር ቤት**" ማለት በግብርና ምርምር እና ልማት ላይ ከተሰማሩ የተለያዩ ግለሰቦች እና ተቋማት ተወጣጥቶ የሚቋቋም የኦሮሚያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ምክር ቤት ማለት ነው።
5) "**መንግሥት**" ማለት የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ማለት ነው።
6) "**ክልል**" ማለት ኦሮሚያ ክልል ማለት ነው።
7) "**ፕሬዝዳንት**" ማለት የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ፕሬዝዳንት ማለት ነው።

8) **"ሴክሬታሪያት"** ማለት የኦሮሚያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን **ሴክሬታሪያት** ማለት ነው፡፡

3. **ጾታዊ አገላለጽ**

በዚህ ደንብ ውስጥ በተባዕታይ ጾታ የተገለጸ ቃል አንስታይ ጾታንም ያካትታል፡፡

4. **የአፈጻጸም ሽፋን**

ደንቡ በክልሉ ውስጥ በግብርና ምርምር እና ልማት ላይ ከተሰማሩ ግለሰቦች እና ተቋማት በሙሉ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

5. **ዓላማ**

ደንቡ የሚከተሉት አላማዎች ይኖሩታል፡-

1) የግብርና ልማት የሚያጋጥሙ ችግሮች የሚለዩበት እና የመፍትሔ ሀሳቦች የሚቀርቡበትን ሥርዓቶች በመፍጠር በክልሉ የግብርና ትራንስፎርሜሽን ውስጥ ድርሻ ያላቸው አካላትን በመለየት ቀጣይነት ያለው መዋቅራዊ ለውጥ እውን ማድረግ፤
2) የምክር ቤቱን አባላት የሥራ ድርሻ እና ግንኙነት በማጠናከር የክልሉ የግብርና ትራንስፎርሜሽን ውጤታማነት እንዲጠናከር ማድረግ፤
3) በክልሉ የግብርና ትራንስፎርሜሽን ሥራ ላይ ሙያዊ ምክር የሚሰጥበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤
4) በክልሉ ውስጥ በግብርና ምርምር እና ልማት ሥራ ላይ ለተሰማሩ የተለያዩ ድርጅቶች ሚናቸው የሚለይበትን ሁኔታ ማመቻቸት እና የተጠያቂነት ሥርዓት እውን ማድረግ፤

## ክፍል ሁለት

### የምክር ቤቱ ምሥረታ፣ ተጠሪነት፣ አደረጃጀት፣ አባላት፣ ሥልጣን እና ተግባር

6. **ምሥረታ**

1) የኦሮሚያ የግብርና ትራንስፎርሜሽን ምክር ቤት ከዚህ በኋላ "ምክር ቤት" ተብሎ የሚጠራ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
2) የምክር ቤቱ ተጠሪነት ለክልሉ መንግሥት ፕሬዝዳንት ይሆናል፡፡

7. **የምክር ቤቱ አደረጃጀት**

ምክር ቤቱ የሚከተሉትን መዋቅራዊ አደረጃጀት ይኖረዋል፡፡

1) የክልል ምክር ቤት
2) ክላስተሮች እና
3) የምክር ቤቱ **ሴክሬታሪያት**

8. **የምክር ቤቱ አባላት**

ምክር ቤቱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡፡

1) የክልሉ መንግሥት ፕሬዝዳንት ............................................................ ሰብሳቢ

2) በምክትል ፕሬዝዳንት ደረጃ የገጠር ልማት ክላስተር ኃላፊ....................ምክትል ሰብሳቢ
3) የግብርና ቢሮ ኃላፊ ......................................................................አባል
4) የኦሮሚያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን አስተባባሪ ....................................ፀሐፊ
5) የኦሮሚያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ...................ረዳት ፀሐፊ
6) የገንዘብ ቢሮ ኃላፊ.......................................................................አባል
7) የፐብሊክ ሰርቪስ እና ሰው ሀብት ልማት ቢሮ ኃላፊ ..........................አባል
8) የመስኖ እና አርብቶ አደር ልማት ቢሮ ኃላፊ ......................................አባል
9) የኮሚኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ ..................................................................አባል
10) የኦሮሚያ ምርጥ ዘር ኢንተርፕራይዝ ዋና ሥራ አስኪያጅ ................አባል
11) የገቢዎች እና ግብርና ምርት ቁጥጥር ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር....አባል
12) የክልሉ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር .............አባል
13) የአከባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ኃላፊ ...................................................አባል
14) የኅብረት ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ ኤጀንሲ ኃላፊ ..........................አባል
15) የክልሉ ግብርና ቢሮ ምክትል ኃላፊዎች .........................................አባል
16) የኦሮሚያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት አማካሪ ቦርድ ................ አባል
17) የግብርና ሚኒስቴር ዴኤታ ...................................................... አባል
18) የኢትዮጵያ ግብርና ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር እና ም/ዋ/ዳይሬክተር..... አባል
19) የኦሮሚያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ም/ዋ/ዳይሬክተር ....................... አባል
20) የኦሮሚያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ረዳት አስተባባሪ ................................ አባል
21) የክላስተሮች ሰብሳቢ እና ምክትል ሳብሳቢ....................................................... አባል
22) የክላስተሮች ፀሐፊ እና ምክትል ፀሐፊ ....................................................... አባል
23) የዞን የግብርና ጽ/ቤቶች እና መስኖ እና አርብቶ አደር ልማት ጽ/ቤቶች ኃላፊዎች.. አባል
24) የስንቄ ባንክ ፕሬዝዳንት ............................................................................... አባል
25) የኦሮሚያ ግብርና ምርምር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተሮች ....................................... አባል
26) በክልሉ የሚገኙ የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተሮች ............. አባል
27) በክልሉ መንግሥት በግብርና ምርምር እና ልማት ላይ የሚሰሩ ዩኒቨርሲቲዎች እና ኮሌጆች ............................................................................................... አባል
28) የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ኃላፊ ............................................................ አባል
29) የሥራ እድል ፈጠራ እና የሙያ ቢሮ ኃላፊ .................................................... አባል
30) የእቅድ እና ልማት ኮሚኒኬሽን ኮሚሽነር ....................................................... አባል
31) የኦሮሚያ አርሶ አደሮች ኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን ............................... አባል
32) የኦሮሚያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ኮርፖሬሽን ዋና ዳይሬክተር ................................ አባል
33) የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት ዋና ሥራ አስኪያጅ እና የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት ኦሮሚያ ቅርንጫፍ ኃላፊ .................................... አባል
34) የኦሮሚያ ከተማ ግብርና ዳይሬክተር ..................................................................አባል
35) በኢንስቲትዩቱ የተመረጡ ከፍተኛ የግብርና ባለሙያዎች ................................ አባል እና
36) ኢንስቲትዩቱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የሚወሰኑ ሌሎች አባላት

## 9. የምክር ቤቱ ሥልጣን እና ተግባር

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የክላስተሮችን ሥራዎች ይከታተላል፤
2. የምክር ቤቱ አባል የሆኑ ተቋማት የማስፈጸም አቅም ያጠናክራል፤
3. የምክር ቤቱን ስብሰባ አጀንዳ ለአባላት እንዲደርስ ያደርጋል፤
4. በክልሉ የልማት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ መሠረት የምርምር ይዘቶች እና በክልሉ የግብርና ልማት ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ እንዲካሄድ የአመራር ምክር ቤት ያማክራል፤ ይረዳል፤
5. በምክር ቤቱ እና ሌሎች አካላት ትብብር እና ቅንጅት በግብርና ቴክኖሎጂዎች አቅርቦት ላይ በግብርና ትራንስፎርሜሽን ውስጥ ሚና የሚጫወቱ አካላትን ያማክራል፤
6. በግብርና ምርምር እና ልማት ሥራ ላይ  መንግሥት ያማክራል፤
7. ክልሉ በግብርና ትራንስፎርሜሽን ላይ ያለውን የቴክኖሎጂ ፍላጎት መነሻ በማድረግ የክልሉን የግብርና ምርምር እና ልማት ተቋማት ይደግፋል፤
8. የክልሉ የግብርና ምርምር እና ልማት ተቋማት በተቀናጀ እና የግብርና ትራንስፎርሜሽን ማጠናከር በሚችል መልኩ የግብርና ምርምር እና ልማት ሥራ እንዲያካሄዱ ይደግፋል፤
9. ለክልሉ የቴክኖሎጂ ፍላጎት ትኩረት በመስጠት ለግብርና ትራንስፎርሜሽን ሥራዎች ድጋፍ ይሰጣል፤
10. የግብርና ምርምር እና ልማት ተቋማት፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ አግሮ ኢንዱስትሪዎች እና የምርምር ውጤቶች ተጠቃሚዎች መካከል ጠንካራ ግንኙነት እንዲፈጠር የተለያዩ መድረኮችን ያስተባብራል፤
11. ሥራውን ከዳር ለማድረስ የሀብት ማስተባበር ሥራዎች ይሰራል፤

## 10. የምክር ቤቱ ሰብሳቢ ሥልጣን እና ተግባር

የምክር ቤቱ ሰብሳቢ የሚከተሉት ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፦

1) የምክር ቤቱን መደበኛ ወይም አስቸኳይ ስብሰባ ይጠራል፤
2) የምክር ቤቱን ስብሰባ ይመራል፤

## 11. የክላስተሮች አደረጃጀት

የክላስተሮች አደረጃጀት አግሮ ኢኮሎጂ እና የግብርና ምርት ሥርዓት ላይ በመመስረት የሚፈጸም ይሆናል። አፈጻጸሙ በሚወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል።

## 12. በምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ የሚሳተፉ ክላስተሮች

የምክር ቤቱን አባላት አስመልክቶ በዚህ ደንብ ውስጥ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከክላስተሮች ውስጥ የሚከተሉት በምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ የሚሳተፉ ይሆናሉ፡፡

1) ከዩኒቨርሲቲዎች፡- የዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት፣የምርምር እና ማህበራዊ ዘርፍ ምክትል ፕሬዝዳንት
2) ከግብርና ምርምር ማዕከል፡- የማዕከሉ ዳይሬክተር እና የኤክስቴንሽን ቡድን መሪ
3) ከዞኖች፡- የዞኖች አስተዳዳሪዎች፣ የዞኖች ግብርና ጽ/ቤት ኃላፊዎች፣ የዞኖች መስኖ እና አርብቶ አደር ልማት ጽ/ቤት ኃላፊዎች እና
4) ኢንስቲትዩቱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የሚወሰኑ ሌሎች አባላት

## 13. የክላስተሮች ተግባር እና ኃላፊነት

ክላስተሮች የሚከተሉት ተግባራት እና ኃላፊነቶች ይኖሯቸዋል፡፡

1) ምርምር ሊካሄድበት የሚገባ የግብርና ምርምር እና ልማት ጉዳይ ይለያሉ፤
2) የምርምር መነሻ ሀሳብ እና ችግርን መሠረት ያደረገ የልማት ሥራ ያቀርባሉ፤
3) ግብርና ልማት ሥራዎችን አስመልክቶ የሚቀርብ የምርምር ፕሮፖዛል እና ጥናት ይገመግማሉ፤ ያፀድቃሉ፡፡
4) የግብርና ምርምር እና ልማት ውጤቶች ይገመግማሉ፤ ያፀድቃሉ፡፡
5) የቴክኖሎጂ ሽግግር ሥልቶችን ይቀይሳሉ፡፡
6) በመስክ ደረጃ የሚካሄዱ ምርምር እና ልማት ይከታተላሉ፤ ይገመግማሉ፡፡
7) በግብርና ምርምር እና ልማት ሥራዎች ውስጥ ባለድርሻ የሆኑትን አካላት ያጠናክራሉ፤
8) ግንኙነት እንዲዳብር እና እውቀት ለመጋራት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ከኢንዱስትሪዎች እና አርሶ አደሮች ጋር ለማስተሳሰር ሥልቶች ይቀርጻሉ፡፡

## 14. የምክር ቤቱ እና የክላስተሮች የስብሰባ ሥርዓት

1) ምክር ቤቱ በክልል ደረጃ በዓመት ሁለት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ የሚኖረው ሆኖ የምክር ቤቱ ሰብሳቢ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡
2) ክላስተሮች በአመት ሁለት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ የሚኖራቸው ሆኖ እንደየአስፈላጊነቱ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡
3) የስብሰባው ቦታ፣ የክላስተሮች ሰብሳቢ እና ምክትል ሰብሳቢ በየዙሩ እነደአስፈላጊነቱ የሚለዋወጥ ይሆናል፡፡
4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1-3 ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ምክር ቤቱ እና ክላስተሮች የራሳቸው የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ማውጣት ይችላሉ፡፡

## 15. የክላስተር ሰብሳቢ እና ፀሐፊ

1) በክላስተር ደረጃ የረጅም ጊዜ ልምድ ያለው የምርምር ማዕከል ለመጀመሪያ ጊዜ የሚካሄደውን ስብሰባ ያስተባብራል፤ ይመራል፤
2) በቂ ልምድ ያለው ባለሙያ ቢያንስ በሥራው ጅምር ደረጃ ላይ ከዩኒቨርሲቲዎች፣ ከምርምር ማዕከል ወይም በጉዳዩ ሁኔታ ላይ በመሞርከዝ ከሌሎች ተቋማት

እያንዳንዱን ክላስተር ለማስተባበር የሚመደብ ሆኖ የክላስተሩ ፀሐፊ ሆኖ የሚያገለግል ይሆናል፡፡

3) በዞን ደረጃ የዞን ግብርና ጽ/ቤት ኃላፊ በዞኑ መዋቅር መሠረት የዞኑ መስኖ እና አርብቶ አደር ልማት ጽ/ቤት ኃላፊ የክላስተር ምክትል ሰብሳቢ ይሆናል፡፡

**16. የክላስተር ሰብሳቢ እና ፀሐፊ ሥልጣን እና ተግባር**

1. የክላስተር ሰብሳቢ የሚከተሉት ተግባር እና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-
   ሀ. የክላስተር ስብሰባ ይጠራል፤ በሰብሳቢነት ይመራል፤
   ለ. ክላስተሩን በበላይነት ይመራል፤
   ሐ. ክላስተር ለማጠናከር ያቅዳል፤ ይሠራል፤
   መ. የክላስተር አባላትን ይከታተላል፤ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤
2. የክላስተር ፀሐፊ የሚከተሉት ተግባር እና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-
   ሀ. የክላስተሮችን የዕለት ተዕለት ተግባራት ያከናውናል፤
   ለ. የክላስተር ዓመታዊ በጀት በማዘጋጀት ለምክር ቤቱ ያቀርባል፤
   ሐ. የክላስተር የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት በማዘጋጀት ለምክር ቤቱ ያቀርባል፤
   መ. የክላስተር ስብሰባ ቃለ-ጉባኤ እና ሌሎች አስፈላጊ ሰነዶች በአግባቡ ይይዛል፤
   ሠ. የክላስተር ውሳኔዎችን አፈጻጸም ይከታተላል፤ ለክላስተሩ ሰብሳቢ ሪፖርት ያደርጋል፤
   ረ. በክላስተር ስብሳቢ የሚሰጡትን ሌሎች ሥራዎች ያከናውናል፤

## ክፍል ሶስት
## የኦሮሚያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ሴክሬታሪያት

**17. ምሥረታ**

1. የኦሮሚያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ሴክሬታሪያት ከዚህ በኋላ “ሴክሬታሪያት” ተብሎ የሚጠራ የኢንስቲትዩቱ አካል ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡
2. የሴክሬታሪያቱ ተጠሪነት ለኢንስቲትዩቱ ይሆናል፡፡

**18. የሴክሬታሪያቱ አድራሻ**

የሴክሬታሪያቱ አድራሻ በአዲስ አበባ ከተማ ኢንስቲትዩቱ ውስጥ ሆኖ እንደየአስፈላጊቱ ቅርንጫፎች ሊኖሩት ይችላሉ፡፡

**19. የመ/ቤቱ አደረጃጀት**

ሴክሬታሪያቱ የሚከተሉትን መዋቅር ይኖረዋል፡፡

1) አስተባባሪ
2) ረዳት አስተባባሪ እና
3) ሌሎች አስፈላጊ ሰራተኞች

**20. የሴክሬታሪያቱ ሥልጣን እና ተግባር**

ሴክሬታሪያቱ የሚከተሉት ሥልጣን እና ተግባር ይኖሩታል

1) በክልሉ የግብርና ትራንስፎርሜሽን ሂደት ውስጥ የግብርና ምርምር እና ልማት ባለድርሻ አካላት ያስተባብራል፤
2) ለፖሊሲ ጉዳይ ወሳኝ የሆኑ ውሳኔዎችን በማስፋፋት የክልሉን የግብርና ትራንስፎርሜሽን ያነቃቃል፤ እንዲፋጠን ያደርጋል፤
3) የትራንስፎርሜሽን አፈጻጸም የሚያበረታቱ እና የሚያሻግሩ ፕሮግራሞች እና ሥራዎች ሥራ ላይ ለማዋል ሁኔታን ያመቻቻል።
4) የግብርና ትራንስፎርሜሽን ሥራዎች በተቀናጀ እና ትርፋማ በሆነ መንገድ ለመሥራት በምክር ቤቱ የተቀመጠውን አቅጣጫ በመከተል የግብርና ትራንስፎርሜሽን ባለድርሻ አካላት ይደግፋል፤ ያስተባብራል፤
5) ምክር ቤቱ በዚህ ደንብ የተሰጠውን ሥልጣን እና ተግባር በአግባቡ እንዲፈጽም ድጋፍ ይሰጣል።
6) የምክር ቤቱ ፀሐፊ ሆኖ ያገለግላል፤
7) የክልሉን የግብርና ትራንስፎርሜሽን መርሃግብሮች የግብርና ምርምር እና ልማት ሥራዎች ያስተባብራል፤ ግብረ-መልስ ይሰታል፤ ለምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል።
8) የምክር ቤቱን የዕለት ተዕለት ሥራዎች ይሠራል፤
9) የሴክሬታሪያቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ሥራዎችን ይፈጽማል።

## 21. የአስተባባሪ ሥልጣን እና ተግባር

አስተባባሪ የሚከተሉትን ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡

1) የሴክሬታሪያቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ ያገለግላል፤
2) በምክር ቤቱ በሚሰጥ አቅጣጫ ላይ ተመርክዞ የሴክሬታሪያቱን የዕለት ተዕለት ሥራዎች ይመራል፤ ያስተዳድራል፤
3) የምክር ቤቱን እና የሴክሬታሪያቱን እቅድ እና በጀት ለመንግሥት ያቀርባል፤ ሲፈቀድ ሥራ ላይ ያውላል፤
4) ሴክሬታሪያቱን ወክሎ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር ውይይት ያደርጋል፤
5) የሴክሬታሪያቱን የሥራ አፈጻጸም እና ፋይናንስ ሪፖርት በማዘጋጀት ለምክር ቤት ያቀርባል፣
6) ከሥልጣን እና ተግባሮቹ መካከል ከፊሉን ለረዳት አስተባባሪ ወይም ለሌሎች ሠራተኞች በውክልና መስጠት ይችላል።

## 22. የረዳት አስተባባር ሥልጣን እና ተግባር

ረዳት አስተባባሪ የሚከተሉትን ሥልጣን እና ተግባር ይኖሩታል፡ -

1. የሴክሬታሪያቱን ሥራ ማቀድ፣ ማደራጀት፣ መምራት እና ማቀናጀት ውስጥ አስተባባሪዉን ያግዛል፤
2. በአስተባባሪው የሚሰጡትን ሌሎች ሥራዎች ይሠራል፤

3. አስተባባሪ በሌለበት እሱን ተክቶ ይሠራል፤

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 23. የምክር ቤቱ እና የሴክሬታሪያቱ በጀት እና የበጀት አስተዳደር

1) የምክር ቤቱ የገቢ ምንጭ መንግስት ለሴክሬታሪያት እና ክላስተሮች ከሚመድበው በጀት ሆኖ እራሱን ችሎ በኦሮሚያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ሥር የሚያዝ ይሆናል።
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሌላ የበጀት ምንጭ ከተለያዩ እርዳታ እና ሥጦታ ሊሆን ይችላል፤
3) የምክር ቤቱ የበጀት አስተዳደር ሁኔታ በመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ሕግ መሠረት ሆኖ የክላስተሮች ድርሻ በሴክሬታሪያቱ የሚከፋፈል ይሆናል፤

### 24. የኢንስቲትዩቱ ሥልጣን እና ተግባር

በሌሎች ሕጎች የተሰጡት ሥልጣን እና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው ኢንስቲትዩቱ፡-

1) ለሴክሬታሪያቱ የሥራ ሁኔታ ያመቻቻል፤
2) በክልሉ የሠራተኛ ሕግ ላይ ተመስርቶ የሴክሬታሪያቱን ሠራተኞች ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤

### 25. ድጋፍ የማድረግ ግዴታ

ለደንቡ ተፈጻሚነት ድጋፍ መስጠት ማንኛውም አካል ግዴታ አለበት።

### 26. ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች

ደንቡን የሚጻረሩ ማናቸውም ተግባራት እና ልማዶች በዚህ ደንብ ውስጥ በተካተቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት የላቸውም።

### 27. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ደንቡን ለማስፈጸም ኢንስቲትዩቱ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

### 28. የደንቡ ሥራ ላይ የሚዉልበት ጊዜ

ደንቡ መጋቢት 23 ቀን 2014 ዓ.ም. ጀምሮ ሥራ ላይ ይውላል።

ሽመልስ አብዲሳ

የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ፕሬዝዳንት

መጋቢት 23 ቀን 2014 ዓ.ም.